ይህ ከዚያድ ህይወት ቀናውና ብሩህ ገጽ ነው። ከዚያም "ተውራትና ኢንጂል ለተቀባዮቹ ምን ጠቀሚቸው?" አሉት። (ቲርሚዚና ሀኪም) ማለትም ዋናው ነገር የቁርዓን መኖር ሳይሆን መነበቡ፣ ትርጉሙ መታወቁና ትዕዛዛቶቹ መከበራቸው ነው። ነብዩ በዚህ መልኩ ነበር ሰዎችን የሚያናግሩት።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ አላህ መንገድ ጥሪ ለማድረግ ወደ ተለያዩ የአረብ ጎሳዎች ይሄዱ ነበር። ወደ ኢስላም እንዲገቡና ለጥሪያቸው ምላሽ እንዲሰጡ ለማበረታታት እጅግ የተዋቡ ቃላቶችን ነበር የሚጠቀመት። ከነዚህ ጎሳዎች አንዱ በኑ አብዱላህ ይባላል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጥሪ ሲያደርጉላቸውና መልዕክታቸውን ሲያቀርቡላቸው "አ በኑ አብዱላህ ሆይ! አላህ ለአባታችሁ ጥሩ ስም መረጠለት" አሉ። ማለትም እናንተ በኑ አብደል ኢዛ ወይም በኑ አብደል ላት አይደላችሁም። ይልቁንም እናንተ በኑ አብዱላህ ናችሁ አሏቸው። ምሲጋና ይግባውና ስማችሁ ውስጥ ኩፍር የለም። ስለዚህ ወደ ኢስላም መግባት አለባችሁ ማለታቸው ነው። በርግጥም ቀጥተኛ ያልሆነ መልዕክት በማስተላለፍ በሰዎች ውስጥ ያለውን አስደናቂ ነገር ማሳየትና ለነሱ ጥሩ እንደሚመኙ የመግለጽ ድንቅ ችሎታ ነበራቸው። ከቀጥተኛ መልዕክቶች ይልቅ ቀጥተኛ ያልሆኑ መልዕክቶች ትልቅ ተጽእኖ አላቸው።

ኻሊድ ኢብኑ ወሊድ (ረ.ዐ) ጀግና ነበር። ተራ ጀግናም አልነበረም። ልበ ሙሉ ጀግና ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኢስላምን እንዲቀበል ይመኙ ነበር። ሆኖም እንዴት? ከሙስሊሞች ጋር በሚደረጉትጦርነቶች ሁሉ ላይ የመካፈል ጉጉት ነበረው። በኡሁድ ጦርነት ወቅት ለሙስሊሞች መሸነፍ ትልቅ ምክንያት የሆነ ሰው ነው። አንዴ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እሱን በተመለከተ "ወደኛ ቢመጣ ከማንም በላይ የሆነ ክብርን እንሰጠው ነበር" አሉ። ይህ ንግግር በሱ ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ አሳደረ? ታሪኩን ከመጀመሪያው ጀምረን እናውሳው። ኻሊድ የካፊሮች ቀንደኛ መሪ ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ኡምራ ለማድረግ ወደ መካ ሲመጡ ኻሊድና ሌሎች የቁረይሽ ጀግኖች ወደ እነሱ በመሄድ አስፋሳን የሚባል ቦታ ላይ አገኟቸው። ኻሊድ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በሲይፍ ወይም በጦር ለመውጋት አስቧል። ስለዚህ ማድፈጥ ጀመረ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጓደኞቻቸው ጋር ሶላት ሊሰግዱ ተነሱ። ይህ ለነኻሊድ ጥሩ አጋጣሚ ነው። ሆኖም ሌላ ችግር ተፈጠረ። የእነሱን ማድፈጥ የተረዱት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአስር ሶላት የአደጋ ጊዜ ሶላት እንዲሆን አዘዙ። ማለትም ባልደረቦቻቸውን ለሁለት ከፈሏቸው። አንዱ ቡድን ከሳቸው ጋር ሲሰግድ ሌላኛው ቡድን ይጠብቅ ጀመር። ይህ ነገር ኻሊድንና ጓደኞቹን አስገረማቸው። እናም ኻሊድ ለራሱ "ይህን ሰው እንዳናገኘው ሆነናል" አለ። ማለትም ከጉዳት የሚጠብቁትና የሚከላከሉለት ሰዎች አሉ ማለት ነው። ከኻሊድና ከጓደኞቹ ለመራቅ ሲሉም ነብዩ ባልደረቦቻቸውን ይዘው ቦታውን በመልቀቅ ሁደይቢያ ላይ ሰፈሩ። ከቁረይሾች ጋር ውል በመፈፀምም በሚቀጥለው ዓመት ለኡምራ ሊመጡ በመስማማት ወደ መዲና ተመለሱ።

ወጥቼ ወደ አረንጓዴ ሰፊ ሜዳ ስሄድ አየሁ። ለራሴም ይሄ ትከከለኛ ህልም ነው አልኩ። ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለመሄድ ስዘጋጅ ከማን ጋር ልሂድ?" ስል አሰብኩ። ሰፍዋን ቢን ኡመያን አገኘሁት። "ኢብኑ ወህብ ሆይ! በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳለን ታውቃለህ? እኛ ልክ እንደ መንጋጋ ጥርስ እርስ በርሳችን እየተፋጨን ነው። በሌላ በኩል ሙሐመድ አረቦችንና አረብ ያልሆኑ ሰዎችን እያሸነፈ ነው። ሙሐመድ ጋር ከተቀላቀልንና ከተከተልነው የሱ ክብር የኛ ክብር ይሆናል" አልኩት። ሆኖም ሰፍዋን በጽኑ ተቃወመኝ። "ሰው ሁሉ ሰልሞ እኔ ብቻ ብቀር እንኳ እሱን አልከተለውም" አለኝና ተለያየን።

ለራሴም "ይሄ ሰው ተጎድቷል። ወንድሙና አባቱ በበድር ጦርነት ወቅት ተገድለውበታል" አልኩ። ወደ ኢክሪማ ኢብን አቢ ጀህል ሄድኩና ለሰፍዋን ቢን ኡመያ የነገርኩትን ነገር ነገርኩት። ሆኖም ሰፍዋን የሰጠኝን አይነት መልስ ሰጠኝ።

ከዚያም ለራሴ ለማንም ሰው ሳልነግር በሚስጥር ወደ ሙሐመድ መሄድ አለብኝ አልኩ። ወደ ቤቴ ሄድኩና መጓጓዣዬን እያዘጋጀሁ ሳለ ኡስማን ቢን ጦለሃን አገኘሁት።

"ኡስማን ጓደኛዬ ነው። ለምን እቅዴን አልነግረውም" ስል አሰብኩ። ሆኖም ከሙስሊሞች ጋር በተደረገው ጦርነት ቤተሰቦቹ ተገድለዋል። ያንን ላስታውሰው አልፈለግኩም። አሁን ልወጣ ስለሆነ ብነግረው ምንም ችግር የለውም አልኩ።

ከዚያም ስለቁረይሽነት ምን እንደማስብ ነገርኩት። "እኛ ጉድጓድ ውስጥ እንደተደበቀ ቀበሮ ነን። ትንሽ ውሃ ወደ ጉድጓዱ ቢለቀቅ ቀበሮው ይወጣል" አልኩት። ወዲያውኑ ሃሳቤን ተቀበለውና ከኔ ጋር ወደ መዲና ለመሄድ ወሰነ። ከዚያም "እኔ ተነስቻለሁ፤ ዛሬ ነው ወደ መዲና ልሄድ ያሰብኩት" አልኩት። ከዚያም የእጁጅ የሚባል ቦታ ላይ ልንገናኝ ተነጋገርን። ቀድሞ ከደረሰ ሊጠብቀኝ ቀድሜ ከደረስኩ ልጠብቀው ተስማማን። ቁረይሾች ጉዞዬን እንዳያውቁ በመፍራት በሌሊት ከቤት ወጣሁ። ጎህ ከመቅደዱ በፊት ከኡስማን ጋር የእጁጅ ላይ ተገናኘን። አልሃዳ ስንደርስ አምር ኢብኑል አስን አገኘነው። "ወዴት ትገሰግሳላችሁ?" አለን።

"አንተስ ከቤትህ ምን አስወጣህ?" አልነው። "እናንተስ ምን አስወጣችሁ?" አለን። "ሙሐመድን ለመከተልና ወደ ኢስላም ለመግባት ፈልገን ነው" አልነው። "እኔንም ያስወጣኝ እሱ ነው" አለ። አብረን ወደ መዲና ሄድን። አንድ ድንጋያማ ቦታ ላይ አረፍን። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የኛን መምጣት ዜና ሰሙ። በጣምም ተደሰቱ። ወደ አላህ መልዕክተኛ የሄድኩት በጣም የሚያምር ልብስ ለብሼ ነው። ወንድሜ መንገድ ላይ አገኘኝና "ፍጠን! የአላህ መልዕክተኛ ያንተን መምጣት ሰምተው በጣም ተደስተዋል። እየጠበቁህ ነው" አለኝ። ፈጠን ፈጠን እያልን መሄድ ጀመርን። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደኛ ሲመጡ ተመለከትኩ። ከርቀት ሲያዩኝ ፈገግ አሉ።

አጠገባቸው እስኪደርስ ድረስ ሳቁ። ሠላም አልኳቸው። ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጡኝ።

"ከአላህ በስተቀር የሚገዙት ጌታ የለም። እርስዎም የአላህ መልዕክተኛ ነዎት" አልኩ። "ቀጥተኛውን መንገድ ለመራህ አላህ ምስጋና ይገባው። አስተዋይ እንደሆንክ አውቃለሁ። አስተዋይነትህ ወደ ጥሩ ነገር እንዲመራህ የዘወትር ምኞቴ ነበር" አሉኝ።

"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በናንተ ላይ ችግር ለማድረስ በተደረገው ነገር ሁሉ ላይ ተሳትፈያለሁ። ምክንያቱም እኔ በሀቁ ላይ ግትር ነበርኩ። አላህ እንዲምረኝ ዱዓ አድርጉልኝ" አልኳቸው። አሳቸውም "ኢስላም ከሱ በፊት የነበሩትን ኃጢያቶች በሙሉ ያስምራል" በማለት መለሱልኝ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እንደሱ እንዲሆንልኝ ዱዓ አድርጉልኝ" አልኳቸው። ከዚያም ዱዓ አደረጉልኝ። "አላህ ሆይ! ሰዎች ከአላህ መንገድ እንዲያፈነግጡ ላደረገው መጥፎ ነገር ሁሉ ኻሊድ ኢብኑ ወሊድን ማረው።" ከዚያ በኋላ ኻሊድ ከኢስላም ዋና ዋና ሰዎች ውስጥ አንዱ ሆነ። የሰለመው ኑብዩ (ሲ.ዐ.ወ) በላኩለት ተዘዋዋሪ መልዕክት ነው። ምን ያህል ብልህና አስተዋይ ሰው ነበሩ ኑብዩ።

አንድ ሱቁ ውስጥ ሲጋራ የሚሸጥ ሰው ካጋጠመህና በዚህ ላይ አስተያየት ልትሰጠው ከፈለግህ የሱቁን ንጽህናና ሌሎች ጥሩ ነገሮች አድንቅለት። ትርፉ እንዲጨምርለትም ዱዓ አድርግለት። ከዚያም ሀላል ገቢ ማግኘት ምን እንደሆነ ጠቁመው። ይህ ከሆነ እሱን አሉታዊ በሆነ መልኩ እየተመለከትከው እንዳልሆነ ይረዳል። ይልቁንም ልምጩን የያዝከው መሃል ላይ ነው። ብልህ ሁን። ያየህበት ጉድለት ተራ እስኪሆን ድረስ የአንድን ሰው ማንኛውም ዓይነት ጥሩ ጎን ፈልግ። ከሁሉም ነገር መጀመሪያ ሰዎች ስላላቸው ጥሩ ነገር አስብ። ስለነሱ ፍትኃዊ መሆንህን እስኪረዱና እስኪወዱህ ድረስ።

በአጠቃላይ...

ሰዎች በጥሩ ጎናቸው ላይ ትኩረት የሰጠነውን ያህል በመጥፎ ጎናቸው ላይ ትኩረት ያልሰጠን መሆኑን ካወቁ ምክራችንን ያደንቃሉ።



ስህተትን ማረም ቀላል ነው

ሰዎች የሚሰሯቸው ስህተቶች ይለያያሉ። አንዳንዶቹ ትልቅ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ትንሽ ናቸው። ስህተቱ ምንም ይሁን ምን ማረም ይቻላል። ምንም እንኳ የአንድን ስህተት መዘዝ ሙሉ በሙሉ ለማረም ባይቻልም ብዙውን ማስተካከል ይቻላል። የራሳቸውን የማረም ብቃት የሚጠራጠሩ ብዙ ሰዎች ስህተታቸውን ማረም ሲያቅታቸው ይስተዋላል። አንዳንዴ የሰዎችን ስህተት የምናይበት መንገድ ራሱ ስህተት ሲሆን ይስተዋላል። ለምሳሌ ልጄ ከተሳሳተ አውግዘዋለሁ፤ አዋርደዋለሁ። ስህተቱን በጣም ከማግዘፌ የተነሳም መውጫ ከሌለው ጉድጓድ ውስጥ እንደገባ አድርጎ ማሰብ ይጀምራል። ከማንኛውም ዓይነት የመታረም እድል ላይ ተስፋ ስለሚቆርጥ በስህተት ላይ ይቆያል።

ሚስቴ ወይም ጓደኛዬ ስህተት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ። በእርግጥም መሳሳታቸውን እንዲያውቁና ከዚያ መውጫ መንገድ መኖሩን እንዲረዱ ካደረግኳቸው እርምት ቀላል ይሆናል። ውሸት ላይ ከማዘውተር ወደ ሐቁ መመለስ የተሻለ ነው። ይህ በእርምት ሂደት ላይ ጠቃሚ መሆኑ ተረጋግጧል።

አንድ ሰው ጉዞ ላይ መሳተፍ የማይችል መሆኑን በመሃላ ሊያረጋግጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣ። "እኔ የመጣሁት መሃላ ላደርስ ነው። ወላጆቼን እያለቀሱ ነው ትቼያቸው የመጣሁት" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አልተቆጡትም። ድርጊቱን አላንቋሸሹም። አስተሳሰቡን አላሳነሱም።

ሰውዬው የመጣው በጥሩ ኒያ ነው። ጥሩ ነገር እንደሰራ አድርጎ ነው ያሰበው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስህተትን ማረም ቀላል እንደሆነ እንዲገነዘብ አደረጉት። እናም "ወደነሱ ተመለሰና እንዳስለቀሰካቸው ሁሉ አስቃቸው" አሉት። ያ ነበር የጉዳዩ መጨረሻ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰዎች ስህተት እየሰሩ እንኳ ቢሆን ቀላል ያደርጉላቸውና ጥሩ ነገሮችን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው ነበር። አንድ መጥፎን ከስተት ላስታውሳችሁ። ምንም እንኳ የዚህ ከስተት ዋና ጉዳይ ያለው መጨረሻ ላይ ቢሆንም ጠቃሚ ነጥቦችን እናገኝበት ዘንድ ታሪኩን ከመጀመሪያ ጀምሬ ላጫውታችሁ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለጉዞ በሚነሱት ጊዜ ሁሌም ለሚስቶቻቸው ዕጣ ያወጣሉ። ዕጣው

"የአቡበክር ልጅ ሆይ! የተናገረውን ነገር አልሰማሽም እንዴ? ዜናው አልደረሰሽም እንዴ" አለችኝ። "ምን ዓይነት ዜና?" አልኳት።

ከዚያም ስም አጥፊዎች የሚሉትን ነገር ነገረችኝ። "ይሄ ነው እንዴ ጉዳዩ?" አልኳት።

"አዎ ይሄ ነው" አለችኝ።

ወላሂ ሽንት ቤት መጠቀም አልቻልኩም። በፍጥነት ወደ ቤት ተመለስኩ። ይብስ ታመምኩኝ። ጉበቴ ለሁለት የተሰነጠቀ እስኪመሰለኝ ድረስ ለቅሶዬን ቀጠልኩ። ለእናቴም "አላህ አውፍ ይበልሽ። ሰዎች ይሄን ሁሉ ነገር ሲያወሩ ለምን አልነገርሽኝም?" አልኳት። እሷም "ልጄ ሆይ! ስለሱ አትጨነቂ። አንዲት ቆንጆ ሴት አለች። የሚወዳት ባል አላት። ሴትዮዋ ጣውንቶች አሏት። ሁላቸውም ከሷ ላይ ስህተት ይፈልጉባታል። ሌሎች ሰዎችም ያንኑ ያደርጋሉ" አለችኝ። "ሱብሃነላህ! ሰዎች የሚያወሩት ይሄንን ነው?" አልኳት።

እንባዬ መቆሚያ አጣ። እንቅልፍ መተኛት አልቻልኩም። እስኪነጋ ድረስ አለቀስኩ።"

አኢሻን የገጠማት ነገር ይህ ነው። በአስራ አምስት አመቷ በዚህ ጉዳይ ላይ ተከሰሰች። በዝሙት ወንጀል። የተከበረችና የታፈረች ሴት ነበረች። በዚያ ላይ ከሰዎች ሁሉ ንፁህ የሆኑት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስት ናት። ከብርና ኩራቷ ተነፍ አያውቅም። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ላይ ወድቃ በወላጆቿ ቤት ሌት ተቀን ታለቅሳለች። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአኢሻ ጉዳይ ችግር ውስጥ ገብተው ነበር። ይህን ጉዳይ ለማብራራት ጅብሪል አልመጣም። ቁርዓንም አልወረደም። ግራ እንደተጋቡ ሰነበቱ። ከመናፊቆች የሚመጡ ክሶች በጣም ብዙና ከባባድ ነበሩ። ሰው ሁሉ ስለሳቸውና ስለሚሰታቸው ብቻ ነበር የሚያወራው። ስቃዱ ሲራዘም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ጉዳይ ላይ ሰዎችን ለማወያዬት ወሰኑ። አላህን አመሰገኑና "በቤተሰቤ ጉዳይ እየገቡ የሚያስቸግሩኝ ሰዎች ምንድን ነው ችግራቸው? ስለ ቤተሰቤ ውሸት እያወሩ ነው። ወላሂ ከነሱ ላይ ጥሩ ነገር እንጂ አላውቅም። በተመሳሳይ ስለ አንድ ሰውም እያወሩ ነው። ወላሂ ከሱ ላይ ጥሩን እንጂ አላውቅም። ከኔ ጋር ሆኖ በስተቀር ብቻውን ወደ ቤቴ ገብቶ አያውቅም" አሉ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ከተናገሩ በኋላ የአል አውስ ጎሳ መሪ የሆነው ሰዕድ ቢን ሙአዝ ተነሳና "የአላህ መልዕክተኛ! እነዚህ ሰዎች የአውስ ጎሳ አባላት ከሆኑ ከድርጊታቸው እናቅባቸዋለን። ከኸዝረጆች ከሆኑ ደግሞ ይዘዙን አንገታቸውን እንቆርጣቸዋለን" አለ። የኸዝረጅ ጎሳ መሪ የሆነው ሰዕድ ቢን ኡባዳህ ይህን ሲሰማ ተነሳ። ምንም እንኳ ጥሩ ሰው ቢሆንም ለእንደዚህ ዓይነት ነገሮች ይሸነፍ ነበር።

"እምላለሁ ዋሽተሃል። አንገታቸው አይቆረጥም። ወላሂ ይህን ያልከው ሰዎቹ የኸዝረጅ ጎሳ አባላት መሆናቸውን ስላወቅከ ነው። ከራስህ ጎሳ ቢሆኑ ኖሮ ይህን አትልም ነበር!" አለው። ይህን የሰማው ኡሰይድ ቢን ኹይደርም በበኩሉ "እምላለሁ ዋሽተሃል። ወላሂ እንገድለዋለን! አንተ ሙናፊቅ ስለሆንክ ነው ለሙናፊቆች የምትከራከረው!" አለው። ከዚያ እርስ በርሳቸው በነገር ይባሉ ጀመር። ሊደባደቡም ደረሱ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚንበራቸው ላይ እንደቆሙ ነው። ዝም እንዲሉ ካደረጉ በኋላ ወደ ቤታቸው ሄዱ። ህዝቡን በማወያዬት ውጥረቱ የማይበርድ መሆኑን ሲረዱ መፍትሄ ለማግኘት ቤተሰቦቻቸውንና የሚቀርቧቸውን ሰዎች ለማማከር ወሰኑ። አሊንና ኡሳማ ኢብን ዘይድን ጠሩ። ኡሳማ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከርስዎ ቤተሰብ ላይ ጥሩ ነገርን እንጂ አይተን አናውቅም። "ይሄ ሁሉ ቅጥፈትና ውሸት ነው" በማለት አኢሻን አሞገሰ። አሊ ደግሞ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ካልሆነ ሴቶች ሞልተዋል። በሷ ፋንታ ሌላ ሚስት ማግባት ይችላሉ። ለማንኛውም ባሪያዋን ይጠይቁ። እሷ እውነቱን ትናገራለች" አላቸው። የአላህ መልዕክተኛ በሪራህን ጠርተው በሪራህ ሆይ! በኢኢሻ ላይ የምትጠረጥሪው ነገር አለ?" በማለት ጠየቋት። "በጭራሽ! ነብይ ኡድን በላከዎት አላህ እምላለሁ! ወላሂ ከሷ ላይ ጥሩ ነገርን እንጂ አይቼ አላውቅም። ልጅ ከመሆኗ ውጪ ከሷ ላይ መጥፎ ነገር አይቼ አላውቅም። ሊጥ አቡክቼ ጠብቂ ስላት እንቅልፍ ይወሰዳትና በፍየሎች ታስበላዋለች" አለች።

የኡማው ትልቁ እውነተኛ ሰው የሆነው አቡበክር ወልዶ ያሳደጋትና ከሰዎች ሁሉ የበላይ የሆኑት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያገቧት አዒሻ እንዴት ነው በመጥፎ ልትጠረጠር የምትችለው? በእርግጥ እንዴት በዚህ ነገር ትጠረጠራለች? የነብዩ የመጀመሪያ ተወዳጅ ሰው ሆና ሳለ? በእርግጥም የአላህ መልዕክተኛ ጥሩን እንጂ አይወዱም። አላህ ምንዳዋን ለመጨመርና ዝናዋን ለማግዘፍ ሲል ሊፈትናት ፈለገ እንጂ።

የኢኢሻ ስቃይ እየጨመረ በርካታ ቀናት ተቆጠሩ። በህመሟና ምግብና መጠጥ በመተዋ ምክንያት የአልጋ ቁራኛ ሆነች። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰዎችን በማወያየት መፍትሄ ለማግኘት ጥረት አደረጉ። ሆኖም ጦርነት ወደ ማስነሳት ተጠጋ። ቤት ውስጥ አሊንና ዘይድን በማወያየት መላ ቢሹም አልተሳካም። ከኢኢሻ ጋር ሊጨርሱት ፈለጉ። እሷም እንዲህ ትላለች። ያን ቀን ያለማቋረጥ አለቀስኩ። መተኛትም አልቻልኩም። በቀጣዮቹ ሁለት ቀናትም አለቀስኩ። አልተኛሁም። ወላጆቼ ያለማቋረጥ ማልቀሴ ጉበቴን ያፈነዳዋል ብለው እስኪጨነቁ ድረስ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አቡበክርን በማስፈቀድ አኢሻን ለመጎብኘት ሄዱ። አኢሻም ከወላጆቿና ከአንዲት የአንሷር ሴት ጋር ነበረች። ሀሜቱ ከተሰማ በኋላ ነብዩ አቡበክር ቤት ሲገቡ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነው። አኢሻን ለአንድ ወር ያህል

አላይዋትም። አኢሻን በተመለከተ የወረደ ነገርም የለም።

የአልጋ ቁራኛ ሆና አገኟት። በማያቋርጠው ለቅሶዋ የተነሳ ላባዋ የተነፈጨ ትንሽ ወፍ ትመስል ነበር። አሁንም እያለቀሰች ነው። ከጎኗ የተቀመጠችው ሴትም አብራት ታለቅሳለች። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቁጭ አሉና አላህን ካመሰገኑ በኋላ "አኢሻ ሆይ! ይህን ይህን ፈፀሙች የሚል ወሬ ደርሶናል" በማለት ከባድ ወንጀል ስለ መፈፀሟ የሚወራውን ነገር ሁሉ ነገሯት። ከዚያም አንድ ሰው ምንም ዓይነት ወንጀል ይስራ ተውበት ማድረግ ቀላል እንደሆነ ሊያብራሩላት ፈለጉ። "ንፁህ ከሆንሽ አላህ (ሱ.ወ) ንፅህናሽን ያውጃል። ስህተት ሰርተሽ ከሆነ ደግሞ ወደ አላህ ተውበት አድርጊ። አንድ የአላህ ባሪያ ጥፋቱን ካመነና ተውበት ካደረገ አላህ ተውበቱን ይቀበለዋል" በማለት ጉዳዩን ሳያወሳስቡና ሳያራዝሙ በቀላል መንገድ አቀረቡ።

አኢሻም "ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግራቸውን ሲጨርሱ እንባዬ ቆመና ወላጆቼ በኔ ፋንታ መልስ እንዲሰጡ እጠባበቅ ጀመር። ነገር ግን አላደረጉም። ለአባቴ "እባክህ ስለተናገሩት ነገር መልስ ስጣቸው" አልኩት። እሱም "ወላሂ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምን ብዬ መልስ እንደምሰጣቸው አላውቅም" አለኝ። ለእናቴም "እባክሽ በኔ ቦታ ሆነሽ መልስ ስጪልኝ" አልኳት። እሷም "ወላሂ ምን ብዬ መልስ እንደምሰጣቸው አላውቅም" አለችኝ። ወላሂ! በዚያን ወቅት እንደ አቡበክር ቤተሰብ ያዘነ ቤተሰብ አልነበረም። ሁለቱም እኔን ወክለው አንድ ቃል መናገር አለመቻላቸውን ሳስብ ይብስ ማልቀስ ጀመርኩ። ከዚያም "ወሬውን እንዳመናችሁ አውቃለሁ። ንጹህ ነኝ ብልም አታምኑኝም። ሃያሉ አላህ ግን ንጹህነቴን ያውቃል። ወንጀሉን ፈፅሚያለሁ ብል ግን ታምኑኛላችሁ። ወላሂ የዩሱፍ አባት ያሉትን ተከታዩን ቃል ከማለት ውጪ ሌላ አማራጭ የለኝም። አልኳቸውና ዞሬ ተኛሁ።

"መልካም ትዕግስት /ከማድረግ ውጪ ሌላ አማራጭ የለኝም።/ ለገለጻችሁልኝ ውሸት እገዛ የምከጅለው ከአላህ ብቻ ነው።" ወላሂ አላህም ንጽህናዬን እንደሚያውጅ አውቅ ነበር። እኔን የሚመለከት ለዘላለም ሲነበብ የሚኖር የቁርዓን አያ ያወርዳል ብዬ ግን አስቤ አላውቅም። አላህ በአንቀጹ ስለኔ ችግር ሊያወራልኝ የሚገባ ሰው አልነበርኩም። ሆኖም ንጹህነቴን ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በህልማቸው ያሳያቸዋል የሚል ግምት ነበረኝ። ወላሂ ከተቀመጡበት ሳይነሱ ሁሌም ወህይ ሲመጣላቸው በሚሆኑበት ሁኔታ ውስጥ ገቡ። አላህ ወህይ አወረደ። ወላሂ አልፈራሁም አልተጨነቅኩም። ምክንያቱም ንጽህናዬን አውቀዋለሁ። አላህም እንደማይበድለኝ እርግጠኛ ነኝ። የአኢሻ ነፍስ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። የአላህ መልዕክተኛ ሲነቁ ወላጆቼ ሰው የሚያወራው ነገር እውነት መሆኑን አላህ ሊያረጋግጥ ይችላል ብለው በመፍራት ነፍሳቸው ልትወጣ ደርሳለች።ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እየሳቁ ፊታቸው ላይ ያለውን ላብ ይጠርጉ ጀመር። "እንኳን ደስ አለሽ አኢሻ ሆይ! አላህ ንጽህናሽን አውጇልሻል" አሉ። "አልሃምዱሊላህ" አልኩ። አላህ ቀጣዩን

የቁርዓን ዓያ አወረደ።

"እነዚያ መጥፎን ውሸት ያመጡ ከእናንተው የሆኑ ጭፍሮች ናቸው። ለናንተ ክፉ ነገር ነው ብላችሁ አታስቡት። በውነቱ እርሱ ለናንተ መልካም ነገር ነው። ከነርሱ /ከጭፍሮቹ/ ለእያንዳንዱ ሰው ከኃጢያት የሰራው ስራ ዋጋ አለው። ያም ከነሱ ትልቁን ኃጢያት የተሸከመው ለርሱ ከባድ ቅጣት አለው። ውሸቱን በሰማችሁት ጊዜ ምእመናንና ምእመናት በጎሶቻችሁ ለምን ደግን ነገር አልጠረጠሩም። ለምንስ ይህ ግልጽ ውሸት ነው አላሉም። በሱ ላይ ለምን አራት ምስክሮችን አላመጡም ምስክሮችንም ካላመጡ እነዚያ አላህ ዘንድ ውሸታሞቹ እነሱ ናቸው።" አላህ እንዲህ በማለትም አስጠነቀቃቸው። "እነዚያ ባመኑት ሰዎች ውስጥ መጥፎ ወሬ እንድትሰፋፋ የሚወዱ ለነሱ በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም አሳማሚ ቅጣት አላቸው። አላህም ያውቃል፤ እናንተ ግን አታውቁም።"

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ህዝቦቻቸው በመሄድ ይህንን የቁርዓን አንቀጽ አነበቡላቸው። ስም አጥፊዎቹንም ቀጡ። ስህተት ላይ የወደቀን ሰው ህክምና እንደሚፈልግ ህመምተኛ ነው ማየት ያለብን። ጉዳዩን ማጋነን፣ እሱን ማውገዝና ለሱ መጥፎ መሆን የለብንም። ምክንያቱም እሱ መጥፎ ነገር በመስራቱ እንደተደሰትክ አድርጎ ማሰብ የሚጀምርበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። ጥሩ ዶክተር ማለት ህመምተኞቹ ለራሳቸው ከሚጨነቁት ይበልጥ የሚጨነቅላቸው ነው።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "የኔና የናንተ ምሳሌ የተቀጣጠለ እሳት አለ። ፌንጣዎችና ቢራቢሮዎች እየሮጡ ይገቡበታል። ይሄኛው ሊከለክላቸው ይታገላል። እኔ ወደ እሳቱ እንዳትገቡ ወደ ኋላ እጎትታችኋለሁ እናንተ ግን ከእጆቼ ታመልጡኛላችሁ" ብለዋል።

አንድ አስተያየት...

አንዳንዴ አንድን ስህተት የምናርምበት ዘዴ ከስህተቱ የበለጠ ትልቅ ስህተት ይሆናል።



ሌላው አስተያየት...

ሰዎች በተፈጥሮና በአካል እንደሚለያዩት ሁሉ በአመለካከታቸው፣ በአስተያየታቸውና በአቀራረባቸው ይለያያሉ። አንድ ሰው እንደተሳሳተ ካወቅክ ምከረው። ስህተቱን ልታርምለት ሞክር። የማያዳምጥህ ከሆነ እንደ አንዱ ጠላትህ አድርገህ አትመዝግበው። ነገሮችን በበጎ መልኩ ተመልከታቸው።

አንድ ጓደኛህን ልታርመው ስትሞክር ምክርህን ቢቃወምህ ጓደኝነትህን ወደ ጠላትነት አትቀይር። ቢያንስ ስህተቱን እንዳይጨምር ተስፋ በማድረግ ለሱ አዛኝ እንደሆንክ ቀጥል።

"ከመጥፎም የባሰ መጥፎ አለ" ይባላል። ሰዎችን በደግነት ከቀረብካቸው ትንሹም ሆነ ትልቁ ስህተታቸው አያስቆጣህም። በደስታ ትኖራለህ። አሚሻ (ረ.ዐ) ስትናገር "ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) በግል ጉዳያቸው የበደላቸውን ሰው ለመበቀል አስበው አያውቁም። ሴትንም ሆነ አገልጋይን በእጃቸው መትተው አያውቁም። በአላህ መንገድ ላይ ሲዋጉ ካልሆነ በቀር። እሳቸውን በግል የበደሏቸውን ሰዎች ተበቅለው አያውቁም። የአላህ ትዕዛዝ ሲጣስ ካላዩ በስተቀር" ብላለች። (ሙስሊም)

ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ይቆጡ እንደነበር ጥርጥር የለውም። ሆኖም ቁጣቸው ለአላህ ነበር። ለራሳቸው ሲሉ አይቆጡም። የሁለቱን ልዩነት መረዳት ይቻል ዘንድ ቁጣዩን ምሳሌ እንመልከት። ትንሹ ልጅህ አንድ ቀን ጠዋት ላይ መጥቶ ለትምህርት ቤት ሁለት ብር ስጠኝ ብሎህ ቦርሳህን ስትከፍት ሙቶ ሙቶ ብር ብቻ ነው ያለህ። ይህ ሙቶ ብር ነው ዘርዝረህ ሁለት ብር ብቻ ውሰድና ሌላውን መልስ ብለህ ሰጠኸው። መልሱን ይዞ እንዲመጣ ደጋግመህ አሳሰብከው። ከአስር በኋላ ወደ ቤት ሲመለስ ሁሉንም ብር አጥፍቶ መጣ። ምን ታደርጋለህ? ምን ያህል ትናደዳለህ? ልትመታው ትችላለህ። ከዚህ በኋላ ሳንቲም የሚባል ላትሰጠው ልትወስን ትችላለህ።

በሌላ ቀን ከአስር በኋላ ወደ ቤት ስትመጣ የአስርን ሶላት መስገዱን ትቶ ጌም ሲጫወት ደረስክ። ባለፈው የተናደድከውን ያህል ነው አሁን የምትናደደው? የመጀመሪያው ቁጣህ የጠነከረ እንደሚሆን አስባለሁ። የአላህ መልዕክተኛ ቁጣ ግን